## በኢሳት የተላለፈው የትግራይ ህዝብን የማጥፋት ጥሪ አጥብቀን እንቃወማለን፣

### *ኢትዮጵያዊያን ተጋሩ የውይይት መድረክ፣*

ታሕሳስ 2017

ኢሳት በትግራይ ህዝብ ላይ ዘርን የማጥፋት ጥሪ በተሌቪዥን ከአንድ ዓመት ከሶስት ወር በፊት አስተላልፎ ስለነበረና መልእክቱ ኢሰብአዊም ወንጀልም ስለሆነ ኢሳት ስህተቱን ራሱ እንዲያርም ይፋዊ ባልሆነ መንገድ፣ በኢሜል በተላከ መልእክት በትህትና ጠይቀነው ነበር፡፡ ከኛ በኩል ይህን ጉዳይ በቅርበት እንዲከታተል በተመደበው አባል በኩል ለአንድ የኢሳት ጋዜጠኛ በ26 ዲሴምበር 2016 ፅፈን፣ ጋዜጠኛውም ማሳሰብያችን ተገቢ እንደሆነና መልእክቱን ለሚመለከተው አካል እንደሚያስተላልፍ ገልፆልን ነበር፡፡

ለብዙ ወራት ጠብቀን ስህተቱ ስላልታረመና በዩትዩብና በሌሎች የብዙሃን መገናኛዎች መሰራጩቱን ስለቀጠለ በ14 ሴፕቴምበር 2017 ለሚመለከተው የኢሳት ኢዲቶርያል ቦርድና ግለሰብ ጋዜጠኞች ከታች የተቀመጠው ደብዳቤ ፅፈንም መልስ አላገኘንም፡፡ በ19 ሴፕቴምበር 2017 ግን አንዲት ጋዜጠኛ የውይይት መድረካችን ከኢሳት ኢዲቶሪያል ቦርድ ጋር ውይይት እንዲያደርግ ሃሳብ ስላቀረበች ሃሳቧን ተቀብለን እነሱ አመቺ ጊዜ እንዳላቸው እስኪገልፁልን ድረስ ጠብቀን ነበር፡፡

በ02 ዲሴምበር 2017 ጋዜጠኛዋ የኢሳት ኢዲቶሪያልና ማነጅሜንት በመሳይ መኮነን የተነበበው መልእክት ይዘቱ ከኢሳት እንዳልፈለቀና ስህተት መሆኑን አይተው ወድያው ያነሱት መሆናቸውን በመግለፅ ጉዳዩን መዝጋታቸውንና ውይይቱን እንደማይፈልጉት እንደነገሯት ገልፃልናለች፡፡ (ከኛ ጋር የሃሳብ ልውውጥ ያደረጉትን ጋዜጠኞች ስሞች ያልገለፅነው ስላላስፈቀድናቸው እንጂ በሌላ ምክንያት አይደለም፤ ለትብብራቸውም እናመሰግናቸዋለን፡፡)

በ1948 በተባበሩት መንግስታት አጠቃላይ ስብሰባ ዘር የማጥፋት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከልና መቅጣትን በሚመለከት በተደረገው ስምምነት [Convention on the Prevention and Punishment of the Crime of Genocide (CPPCG)] መሰረት አንድ ሰውም እንኳን ባይገደል አንድ ህዝብን በሙሉ ወይም በከፊል የማጥፋት ዓላማ ያለው ጥሪ በወንጀል ያስከስሳል። ኢሳት ባስተላለፈው ጥሪም የትግራይ ህዝብን የማጥፋት አላማውን በይፋ ገልፀዋል፡፡ እኛ የምንለው ማንም ሓላፊነት የሚሰማውና የሚያመዛዝን ግለ ሰብ ይሁን ተቋም በየትም ቦታ በተራ ህዝብ ላይ እልቂት እንዲፈፀም መቀስቀስ ፈጽሞ የለበትም ነው፡፡ ባገራችን ከ66ቱ አብዮት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የብዙ ዜጎች ህይወት በመቀጨት ላይ ነው፤ <u>ይሁን እንጂ በታሪካችን ውስጥ ያንድ ብሄር ህዝብ እንዲደመሰስ ጥሪ ያስተላለፈ ተቋም ኢሳት ብቻ ሆነዋል</u>።

የኢሳት ኢዲቶሪያልና ማነጅሜንት መልእክቱ ስህተት መሆኑን ከልብ ካመኑ ለኛ በጋዜጠኛዋ በኩል እንዳስነገሩን ጥሪውን ላስተላለፉለት ህዝብ የጥሪው ስህተትነት በይፋ ነግረው ለትግራይ ህዝብም ይቅርታ

መጠየቅ አለባቸው ባዮች ነን፡፡ ጋዜጠኞቹ የማያውቁት፣ ያልገባቸውና ህዝብ እንዲቀበላቸው የማይፈልጉት መልእክት እንደሚያስተላልፉ ማመን አይቻልም፡፡

ስለሆነም ኢትዮጵያዊያን እንዲገነዘቡትና የራሳቸው ፍርድ እንዲሰጡበት የኢሳት ጥሪንና እኛ ኢሳት ጥሪውን በይፋ እንዳሰራጨው በይፋ እንዲያርመው በማሳሰብ የፃፍንለትን ውስጣዊ ደብዳቤ እንደሚከተለው በግልፅ አውጥተነዋል፡፡

ሀ. የኢሳት ጥሪ :

አቶ መሳይ መኰንን በኦገስት 6፣ 2016 በኢሳት ቴሌቪዥን ያስተላለፈው የትግራይ ህዝብ የማጥፋት ጥሪ የሚከተለው ነበር፡

"እንደምታዩት እኛን የገጠመን ትግል በማንኛውም ዓለም እንደሚከሰተው በጨቋኝ መንግስትና በተጨቋኝ ህዝብ ተብሎ በሚጠራ መካከል ሳይሆን በአንድ ዘራችሁን በማጥፋት የበላይ ሆኜ ልግዛ በሚል ጎሳና ፍዳው አላልቅ ባለው ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ መካከል ነው፡፡

የኢትዮጵያ ወገናችን ሆይ፣ ይህ የጥፋት እቅድ የታቀደው ከአምስት ሚልዮን ህዝብ ለ95 ሚልዮን ህዝብ ነው፡፡ ለዚህ ወደደንም ጠላንም ምርጫው አንድ ብቻ ነው፡፡ እነሱ ወደፈለጉት የሃይል እርምጃ በመግባት ነፃነትን ማስመለስ፡ የተበላሸን ዓሳ ከባህር ማስወገጃ መንገዱ አንዱ ነው፡ የባህር ውሃን ማስወገድ፡፡" (ሰረዝ የተጨመረ)

ለ . የኛ የውስጥ መልእክት ለኢሳት :

የተከበራችሁ የኢሳት ኤዲቶሪያል ቦርድና ጋዜጠኞች፣

አስቀድመን የማክበር ሰላምታችንን እናቀርብላችሁ አለን፡፡

እስካሁን ድረስ የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ በህዝባችን ላይ የሚፈፅማቸውን ግፎች በማጋለጥና የታፈነው ህዝባችን መረጃዎች እንዲያገኝ በማድረግ የምትጫወቱት ሚና ማንም ሌላ ኢትዮጵያዊ ተቋም ከሚያደርገው የላቀ ነው፡፡ ይህንንም ድርጊታችሁ እንድትቀጥሉበት ልናበራታታችሁና ልንተባበራችሁ እንደምንፈልግ ልንገልፅላችሁ እንወዳለን፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ፣ እናንተ ስህተት ስትፈፅሙ ደግሞ እንደ ወገን ስህተታችሁን እንድታርሙ ልናሳስባችሁ እንፈልጋለን፡፡ ይህንን ደብዳቤ የፃፍንላችሁም ለዚህ ዓላማ ነው፡፡ ስህተታችሁን እንድታርሙ በተለያዩ ወገኖች ማሳሳብያዎች ቀርበውላችሁ ነበር፤ ሆኖም ከአንድ ዓመት በላይ ሳታርሙ ቆይታችሁዋል፡፡ ስለዚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን መልእክት በይፋ እንዳስተላለፋችሁት በይፋ ባለማረማችሁ ይህንን ደብዳቤ ልንልክላችሁ ተገደናል፡፡

የህወሓት ባለስልጣኖች ሌሎች ራሳቸው የመሰረቷቸው አሻንጉሊት የኢህአደግ አባል ድርጅቶችን እንደ መሳሪያ በመጠቀም ለዘመናት አብሮ የኖረውን ህዝባችን በነገድ እየከፋፈሉ በመግዛት የህዝባችንን አንድነት ለአደጋ በማጋለጣቸው እናወግዛቸዋለን፡ እንደዚሁም በአጠቃላይ በሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ በተለይ ደግሞ በኦሮሞ፣ አማራና በኮንሶ ለፍትህ የሚደረጉትን የህዝብ ተቃውሞዎች በመደገፍ በህወሓት ባለስልጣኖች ወሳኝነት የሚፈፀሙትን የግድያና የእስር እርምጃዎች እናወግዛለን፡፡ ከዚህ በፊትም በተደጋጋሚ ባወጣናቸው መግለጫዎች የህወሓት/ኢህአደግ ጭፍጨፋዎችን በማውገዝ በተግባር አሳይተናል፤ ለወደፊቱም እንቀጥላለን፡፡

ከ26 ዓመታት በላይ በህወሓት የበላይነት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ሰፍኖ ያለው አረመኔያዊ አገዛዝ ካልተወገደ የህዝባችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማስከበር፣ የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ፣ ሙስናን ለማጥፋት፣ ያገራችን አንድነት ዋስትና እንዲኖረው ለማድረግና ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ለመገንባት የሚቻልባቸው ሁኔታዎች እንደሌሉ እንገነዘባለን፡፡

በትጥቅ ትግሉ ጊዜ የህወሓት ባለስልጣኖች በትግራይ ህዝብ ላይ ከደርግ የባሱ የግድያ ወንጀሎች እንደፈፀሙ ማስታወሱ እነዚህ ሰዎች የማንም ህዝብ፣ የትግራይ ህዝብም ቢሆን ወዳጅ እንዳልሆኑ ለመገንዘብ ይረዳል፡፡

ሆኖም የህወሓት ባለስልጣኖች የትግራይ ህዝብን ከ40 ዓመታት በላይ አፍነው እየጨፈጨፉ፣ አማራጭ ሃሳቦች እንዳይሰማና በነፃነት ራሱን እንዳያደራጅ ከልከለው በጉልበት የነሱን አስተሳሰብና አሰራር ተሸማቅቆ እንዲከተል አስገድደውታል፤ በያለበት በዘውግ እንዲደራጅ በማድረግም ከፋፍለው ለመግዛት ተጠቅመውበታል፣ አሁንም እየቀጠሉበት ነው፡፡

የትግራይ ህዝብ በሙሉ የህወሓት ባለስልጣኖች የሚነግሩትን ያምናል፣ ይቀበላል ማለት አደለም፤ ስለታፈነና እርስ በርሱ እንዳይተማመን ስለተደረገ ግን ነፃ ሆኖ ስሜቱንና ትክክለኛ ፍላጎቱን መግለፅ አይችልም፡፡ አገዛዙን ከሚደግፉ ሰዎች ውስጥ ከስርአቱ ጋር በጥቅም የተሳሰሩ አሉ፤ በጠባብ ብሄራዊ ስሜትና በድንቁርና የሚደግፉ አሉ፤ በፍርሃትም የሚደግፉ አሉ፡፡

እናንተ ከኢትዮጵያውያን ውስጥ እንደ ጠላት የምታዩት ህዝብ ሊኖር እንደማይችል እናምናለን፡፡ በደብዳቤው መጀመሪያ ላይ እንደጠቀስነው ባለልረባችሁ አቶ መሳይ ያስተላለፈው መልእክት ግን፡

1. ከእውነት የራቀ ነው፤ ምክንያቱም አቶ መሳይ "ዘራችሁን በማጥፋት የበላይ ሆኜ ልግዛ በሚል ጎሳ" የሚለው ህፃናትና ፊደል ያልቆጠሩ አርሶ አደሮችን ያካተተ ነፃነት የሌለው የትግራይ ህዝብ የወገኑን ዘር ለማጥፋትና ለመግዛት እቅድ ሊያወጣ እንደማይችል አቶ መሳይም እያውቀ ሌሎች ኢትዮጵያውያን እንዲቀበሉት ያስተላለፈው መልእክት መርዝ ነው።

2. ህዝባችንን እንደ ጠላት እንዲተያይ የሚያደርግ ነው፤ ምክንያቱም አቶ መሳይ ያስተላለፈው መልእክት 95 ሚልዮኑ የኢትዮጵያ ህዝብ የትግራይ ህዝብን እንደ ጠላት እንዲያይ የሚያደርግ ነው፡፡

3. የእልቂት ጥሪ ነው፤ ምክንያቱም አቶ መሳይ የትግራይ ህዝብን "ዘራችሁን በማጥፋት የበላይ ሆኜ ልግዛ እንደሚል ጎሳ" ከፈረጀ በኋላ ለዚህ መፍትሄው የባህር ውሃን ማስወገድ እንደሆነ ሲገልፅ፣ ህዝብን ከባህር ጋር ማመሳሰል የተለመደ ስለሆነ የትግራይ ህዝብ እንዲደመሰስ ያቀረበው ጥሪ ነው፡፡

ኢሳት አቶ መሳይ ያስተላለፈውን መልእክት ስላልደጋገመ መልእክቱን የመተግበር ዓላማ እንደሌለው ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ በመገናኛ ብዙሃን የተላለፈ መልእክት ከላኪው ቁጥጥር ውጭ እየተራባ ይሰራጫል፤ አምነውበት ወደ ተግባር ሊተረጉሙት የሚፈልጉ ሰዎችም ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ እሳት በአቶ መሳይ አማካይነት ያስተላለፈው መልእክት ስህተት እንደሆነ በመግለፅ ራሱን ከታሪክ ተጠያቂነት ማዳን አለበት፡፡

አንድ ሰፊ ህዝብን እንደ ጠላት ፈርጆ መቀስቀስ ሊያስከትለው የሚችለውን የእልቂት አደጋ ከታሪክ ግንዛቤ መውሰድ ያስፈልጋል፡፡

ይህንን ከኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ የአንዱን ነገድ/ዘውግ ህዝብን የማጥፋት ቅስቀሳ እንኳንና ለኢትዮጵያ ህዝብ መብት ከሚታገል ተቋም ይቅርና በግልፅ ፋሽስት ከሆኑ ሃይሎችም ማስተላለፍ በመጀመሪያ በወንጀል

ስለሚያስጠይቅ፣ ሁለተኛ ደግሞ በጣም ስለሚያሳፍር በያዝነው የ21ኛ ክፍለ ዘመን በየትኛውም አገር ላይ ሊደረግ የሚገባ ቅስቀሳ አይደለም፡፡ አቶ መሳይ ሲጀምር ህሊናው ፈቅዶለት ሳይዘገንነው እንዴት ያንን መልእክት እንዳስተላለፈ ለማመን ያስቸግራል፤ ስህተቱን በቀላሉ ማረም እየቻለም አለማረሙ እንደተሳሳተ አለማመኑን ያመለክታል፡፡ ከሁሉም የባሰው ደግሞ በእሳት የሚተላለፉትን መልእክቶች ይዘት የመወሰን ስልጣን/ድምፅ ያላችሁ ሰዎች ይህንን ስህተት በይፋ ባለማረማችሁ ስህተቱን የጋራ አድርጋችሁታል፡፡

የኢሳት ጋዜጠኞች ብዙ ጥሩ ስራዎች እያካሄዳችሁ በተፈፀመው ስህተት ታሪካችሁ ከ’ዘር ማጥፋት ቅስቀሳ’ ጋር እንዲያያዝ ህሊናችሁ ሊፈቅድላችሁ አይገባም፤ ስለዚህ ስህተቱን በይፋ እንዳስራጫችሁት በይፋ እንደምታርሙና ራሳችሁን ከዚህ ታሪካዊ ስህተት እንደምታላቅቁ በማመን ይኽን አጭር ደብዳቤ ፅፈንላችኋል፡፡

***ኢዮጵያዊያን ተጋሩ የውይይት መድረክ።***